**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ጥር 18 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**ወያኔ በአዲስ አበባ ብጥብጥ ለማነሳሳት ውስጥ ውስጡን እየሰራ ነው፣ ከ12 ዓመት በላይ ግብር የተከፈለባቸው ከ8 ሽህ የሚበልጡ ቤቶችም ሊንድ ነው፣ የኮሌጅና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችም የየዕምነታቸውን ሥርዓት በወጉ እንዳያከናውኑ ታገዱ፣ የኢንተርኔት ካፌ ባለንብረቶችም የደህንነት ሥራ እንዲሰሩ ተገደዱ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ለማንበብ እዚህ ይጫኑ.......................**

የወያኔው ከፋፋይ ቡድን በጅማ፣ በአጋሮ እና በደቡብ ክልል ውስጥ የጀመረው እርስ በእርስ ማጋጨት በርዕሰ መዲናዋም ለማቀጣጠል ሰሞኑን ሌላ አዲስ ሰልት ቀይሶ እየተቀንቀሳቀሰ መሆኑ ተጋለጠ::

ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ትምህርት ቤቶችና መስጊዶች አካባቢ ተንቀሳቅሶ ለመከታተል ባደረገው ሙከራ መሠረት ከጥር 5 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በህቡዕ ወረቀት እየተበተነ ቅስቀሳ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ችሏል::

በሙስሊሙ ሕብረተሰብና በክርስትናው አማኞች መካከል ለዘመናት ተባብረውና ተቻችለው አልፎ ተርፎ ተዋድደው የኖሩበት ከተማ አዲስ አበባን ዛሬ የወያኔ ቡድን በዘረጋው የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ምክንያት ሰሞኑን ሁለቱን ሕብረተሰብ ሊያጋጭ የሚችል ከንቱና ባዶ ፕሮፓጋንዳ የሆነ ፅሁፍ በህቡዕ በትምህርት ቤቶችና በመስጊዶች አካባቢ እየበተነ ሙስሊሙን ሕብረተሰብ የሚያስቆጣና ብጥብጥ እንዲነሳ እያደረገ መሆኑንም ከተለያዩ የሙስሊም አማኞች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል::

በተለይም በየትኛውም ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ሴቶቹ ሂጃባ (ሻሽ ማሰር) ወንዶቹ ስግደት እንዳያደርጉ በየርዕሰ መምህራኖቹ ትዕዛዝ የተላለፈ ሲሆን፣ ለክርስትና እምነት ተከታይ ተማሪዎችም ምሳ በሚበሉበት ሰዓት ፀሎት እንዳያደርጉ መከልከሉን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተለይም የሙስሊም አማኝ ተማሪ ቤተሰቦች በየትምህርት ቤቱ በመገኘት ለምን ይህ እንደሆነ ቢጠይቁም አጥጋቢ ምላሽ ለማግኘት እንደልቻሉና ከትምህርት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ትዕዛዝ እንደወረደ እና ይህንኑ ተግባራዊ እንዲያደርጉ መታዘዛቸውን የየትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምህራን መግለፃቸው ታውቋል ::

የወያኔው ዘረኛ ቡድን በጅማ በ1999 ዓ.ም በጥቅምት 5 ቀን የሙስሊምና የክርስትና እምነት ተከታዮችን እርስ በእርስ አጋጭቶ ከፍተኛ እልቂት እንዲከሰትና በርካታ ሰዎች ሕይወት እንዲቀጠፍ ቤት ንብረታቸው እንዲወድም ከማድረጉም በተጨማሪ የእምነት ቦታዎች እንዲጋዩ ካደረገ በኋላ መልሶ ሽማግሌ፣ ከሳሽና ቀጪ ሆኖ ብቅ እንዳለው ሁሉ ዛሬም በአዲስ አበባ ውስጥ የሙስሊሙን ሕብረተሰብ ቁጣ

ለመቀስቀስ በማሰብ የሚበተን ወረቀት በየመስጊዱ እና በየትምህርት ቤቱ ግቢ እየበተነ «የሙስሊም ተማሪዎች ሂጃባ ማድረግ የለባቸውም፣ ተማሪዎች ሰላት መስገድ የለባቸውም የክርስትና እምነት ተከታይ ተማሪዎችም ፀሎት ማድረግና ማንኛውንም የእምነት እንቅስቃሴ ማድረግ ማቆም አለባቸው . . . » የሚሉና ሌሎችንም አካትቶ እምነቱ የሚፈቅደውን ሁሉ በመፃረር የሚገልፅ ወረቀት እየበተነ በመሆኑ የእምነቱ አማኞች በእጀጉ በመበሳጨት ላይ መሆናቸውም ታውቋል።

አንዳንድ የእምነቱ አባቶች የዕድሜ ባለጠጐች ሁኔታውን በአንክሮ እየተከታተሉ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ስህተት ላይ እንዳይወድቅ ውስጥ ውስጡን እየመከሩ በመሆኑ ችግሩ እስከ አሁን ሊከሰት እንዳልቻለ የደረሰን ዘገባ ገልፆ ወያኔ ግን አሁንም ከድርጊቱ ሳይታቀብ በየቀኑ ጧትና ማታ ላይ ወረቀት እየበተነ ቅስቀሳ እያደረገ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቷል።

አንድ የእምነቱ አባት ለተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን እንደገለፁት ከሆነ «ይህን ድርጊት ማን እንደፈፀመው ሳናውቅ ለሁለትና ሶስት ቀን ያህል ስንበሳጭ ነበር። ነገር ግን ከዚያ በኋላ በወያኔ ደህንነቶች እየተሰራ መሆኑን ጠንቀቀን ስንረዳ ልጆቻችንም ቤተሰቦቻችንም ስህተት ውስጥ እንዳይወድቁ እየነገርናቸው ሁኔታውን ልናበርደው ችለናል። የሆነው ሆኖ ግን አሁን በዚህ ምክንያት ብጥበጥ እንዲነሳ አድርገው መልሰው የሚፈልጉትን ነጋዴ እየለቀሙ ካስገቡ በኋላ ሽማግሌ፣ ከሳሽ፣ አሳሪና ቀጪ ሆነው ሊቀርቡ እቅድ መኖሩን ተረድተናል። እናም ሁኔታው ስለገባን ምንም አይነት ብጥብጥ እንዲነሳ አናደርግም። ነገር ግን በሕጋዊ መንገድ ወኪሎቻችንን ልከን ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሠላማዊ ሰልፍ ፈቃድ ጠይቀን ድርጊቱን ለማውገዝ በዝግጅት ላይ ነን» በማለት አስረድተዋል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳዋን የሰላማዊ ሰልፍ ፈቃዱን ሕዝቡ ቢጠይቅም ሕዝብ የሚፈራው ወያኔ የሠላማዊ ሰልፉን ፈቃድ ሳይሰጥ መቅረቱ ታውቋል።

የሸዋ ዳቦ በሚባል የሚታወቀው ዳቦ ቤት የአንድ ብር ሶስት እየሸጠ ባለበትና የአንድ ሌትር ነዳጅ ዋጋ 10 ብር በሆነበት የኑሮ ውድነቱ ከጣራ በላይ በዘለለበት በዚህ ወቅት ሕዝቡ ስለ ኑሮው እንዳያስብና እንዳያማርር ሌላ ስልት ነድፈው ሕዝቡን ለማበጣበጥ መሞከራቸው የእነ መለስ ዜናዊ ስሌትና የደህንነቱ ስራ አስቀድሞ ከጅምሩ ሳይጀመር የተጠናቀቀ ድራማ መሆኑን ተረድተናል ያለው ሌላው አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ሕብረተሰቡ ለእንዲህ ላለ ርካሽ የፖለቲካ ሥራ እንዳይታለል ሲልም ጥሪ አስተላልፏል።

ከዚህ ቀደም የአዲስ አበባ ከተንቲባ ሆኖ የተሾመው አሊ አብዶ በነበረበት ወቅት የኦርቶዶክስ እምነት ይዞታ የነበረውን ከአየር ጤና ወደ አለም ባንክ በሚወስደው መንገድ ላይ የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ቦታ ለሙስሊም ወንድሞቹ መስጊድ

መስሪያ በሚል ሰጥቶ ጥቂት የወያኔ ሴራ ባልገባቸው የሁለቱም እምነት ተከታዮች መካከል በተከሰተ ግጭት ከሁለት ሰዎች ያላነሱ ለሞት የተዳረጉ ሲሆን፣ ችግሩን የሁለቱ እምነት አርቆ አስተዋይ ሽማግሌዎች ተወያይተው መፍትሄ በመስጠታቸው ዛሬ መስጊዱም ተሰርቶ የጥምቀት በዓሉም በዚያው ቦታ ተከብሮ ሕዝቡ ድሮ ወደነበረበት ፍቅር ተመልሶ የሚገኝ መሆኑን የጠቀሱት አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ይህ አልሳካ ያላቸው ወያኔዎች ዛሬ ደግሞ የጅል ስልት ይዘው ቀርበው ሲንገታገቱ መታየታቸው አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ሲሉም ገልፀዋል።

እነ ሼህ ኤሊያስ ሬድዋን የእስልምና ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት በአንዋር መስጊድ ብጥብጥ እንዲነሳ አድርገው በርካታ የእምነቱ ሰዎች ታፍሰው ሲታሰሩና በወቅቱ የነበሩት የእስልምና ጉዳዮች ፕሬዝዳንትን ጨምሮ ብዙ አባቶች ዘብጥያ እንዲወርዱ ካደረጉ በኋላ እነሱ ስልጣን ላይ ተቀምጠው ስለራሳቸው ሕይወትና ስለ ወያኔ የስልጣን እድሜ እንዲያረዝምላቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የካድሬነት ስራ እየሰሩ ተቸግሮ ያለውን የሙስሊሙን ሕብረተሰብ ግን ለመርዳት አንዳችም ሙከራ የማያደርጉ ሰዎች ዛሬ ይህ ችግር እንዲነሳ ከወያኔ ደህንነቶች ጋር በመሆን እየሰሩ መገኘታቸው በጣም አሳዛኝ ነው የሚሉ በርካታ የእምነት ተከታዮች ናቸው።

የወያኔ ቡድን በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ ኮሌጆችና ት/ቤቶች ውስጥ ማንኛም የእምነት ሥነ ሥርአት እንዳይካሄዱ በየትምህርት ሚኒስትር ተብዬው መስሪያ ቤት በኩል ባስተላለፈው ጥሪ መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ ከሳምንት በፊት ደብዳቤ ወጪ ተደርጐ የተሰጣቸው መሆኑን የገለፀው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ ጥር 5 ቀን 2000 ዓ.ም ዋቢ ሸበሌ ጉን በሚገኘው የቅድስተ ማሪያም ካምፓስ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ደብዳቤው ሲነበብላቸው በመቃወም ከፍተኛ ረብሻ አንስተው በፖሊስ ኃይል እንደቆመ አረጋግጠዋል።

የወያኔ ቡድን የሚዘይዘውንና የሚጨብጠውን ሲያጣ በአንድ ጀንበር ሕግ የሚያወጣ ደፋርና ማገናዘብ የተሳናቸው የተሰባሰቡበት ቡድን በመሆኑ ዛሬ በኃይማኖት ተቻችሎ አንተ ትብስ አንተ ተባብሎ የኖረውን ሕዝብ እምነቱን ጠብቆ በስነ ምግባር የታነፀ ዜጋ ለማፍራት እንዳይችል ሆን ብለው ይህን የመሰለ ትዕዛዝ ማውታጣቸውና ብሎም ለየትምህርት ቤቶቹ ትዕዛዝ ማስተላለፋቸው በሐገሪቱ ሠላም እንዳይሰፍንና በጥብጥ ተነስቶ እንደተለመደው የዜጐች ደም በአውላላ ሜዳ ላይ እንዲፈስና ጭዳ ለማድረግ አስበው ነው ያሉት የቅድስተ ማርያም ኮሌጅ መምህር የተሰጠን ትዕዛዝ ከውሃ የቀጠነ በመሆኑ ሳንወድ በግድ መልዕክቱን ልናስተላልፍ በቅተናል። አሁን ግን ቀድሞ በነበረው መንፈስ ማስተማሩና መማሩ የሚቀጥል

አይመስለኝም በአንድ ሳምንት ጊዜ ብዙ ተማሪዎች እየቀሩ ናቸው ነገ ደግሞ ምን እንደሚከሰት አናውቅም ሲሉ እኚሁ መምህር ያላቸውን ስጋት በአፅንኦት ገልፀዋል፡፡

እንዲህ ያለ ሴራ በወያኔ ቡድን እየተጠመጠመ ባለበት ሰሞን ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አሙዲአስ የተባለ ለወያኔ ቅርበት ያለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው የተባለው ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ «በኢትዮጵያ የኃይማኖት መቻቻል ምን ይመስላል?» በሚል በተካሄደው ውይይት ላይ እጅግ አስደንጋጭና ወደፊትም አደገኛ አዝማሚያ የሚፈጥር ሐሳብ ከአንድ ምሁር ተብዬ ግለሰብ አስተያየት ሲሰጥ መደመጡና በውይይቱ ላይ ያሉትን ምሁራኖች ያስደነገጠ እንደነበር ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፕሮፌሰር ሁሴን አህመድ የተባለው ምሁር ነኝ ባይ ወያኔ እንደገለፀው ከሆነ «በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም አይነት የኃይማኖት መቻቻል የለም» በማለት ወያኔ የሚያራግበውን ርካሽ ፖለቲካ በመድገም ከዚህ ቀደም በሀገሪቱ የኃይማኖት መቻቻል እንደሌለና ወደፊትም እንደማይኖር መግለፁ በእጅጉ አሳዛኝና አሳፋሪ መሆኑን በውይይቱ ላይ የተገኙ ምሁራኖች አፅንኦት ሰጥተው ሲከራከሩ እንደነበርም የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

ፕሮፌሰር ሀሰን የተባለው ይኸው ወያኔ ዘራሽ ግለሰብ ወያኔ በሕዝቦች መካከል መጠላለፍና መተላለቅ እንዲኖር ሌት ተቀን እየሰራ ያለውን ሥራ በማጠናከር ለዘመናት ተዋልዶና ተዋድዶ ያለውን ሕዝብ በኃይማኖት ሰብብ ግጭት እንዲቀሰቀስ ለማድረግ አቋም ይዞ ሲከራከር ምሁራኖቹ ያዘኑም ከመሆኑም ባሻገር እንዳፈሩበት በግልፅ የተናገሩ መሆኑን የገለፀው ዘገባው ከወያኔ እንዲህ አይነት ርካሽ ተወዳጅነት ለማግኘት በሚጥሩ ግለሰቦች አማካኝነት በሕዝቦች መካከል ክፍተት እንዲፈጠር እየጣረ መሆኑን ሕዝቡ እንዲያውቀው ሲሉም በውይይቱ ላይ የተገኙ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖች ገልፀዋል፡፡

በዕለቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የኃይማኖት መቻቻል እንዳለና ወደፊትም ወጣቱ ትውልድ ይህንኑ አጠንክሮ መያዝ እንዳለበት አፅንኦት ሰጥተው ከተከራከሩት መካከል ዶ/ር አህመድ ሁሴን የተባሉ ምሁር እንደሚገኙበትም ዘገባው ገልጿል፡፡

የወያኔ በድን በሠላም ተፋቅሮ የኖረውን ሕዝብ ለማበጣበጥ ላይ ታች በሚልበት በዚህ ወቅት በአዲስ አበባ በተለያዩ የምድር ጦር መምሪያዎች ያሉ መስመራዊ መኮንኖች እና ወታደሮች ባለሥልጣናቱን በጥያቄ ማጣደፋቸውን የመከላከያ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡

ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ ውስጥ የተለያዩ የመምሪያ ቢሮዎች ውስጥ የሚሰሩ ከሻምበል ማዕረግ እስከ ተራ ወታደር ድረስ ያሉ የጦር አባት አንድ ላይ በመሰባሰብ በመኮንኖች አዳራሽ ባካሄዱት ስብሰባ ላይ እንዳስታወቁት «በሱማልያ

ውስጥ ገብቶ በየቀኑ እየሞተ ያለው ኢትዮጵያዊ የስቃዩ ቀን መቆም አለበት ስለዚህ በአስቸኩዋይ ሞቃዲሾንና አካባቢዋን ለቅቆ ወደ ድንበራችን እንዲገባ ትዕዛዝ ይተላለፍለት» በማለት ለወያኔ ባለሥልጣናት አስጨናቂ ጥያቄ የጦሩ አባላት በማንሳታቸው የተደናገጡት ጄኔራሎች ለጊዜው ከማን ጋር በስልክ እንደተገናኙ ለማወቅ ባይቻልም «ከ6 ወር በኋላ ይህ አሁን ያነሳችሁት ጥያቄ ተግባራዊ ይሆናል:: ስለዚህ ወገኖቻችን ይህንን እኛ ሳንረዳው ቀርተን ሳይሆን ሀገራችን በታሪኩዋ እንዲህ ያለ ሽንፈት ገጥሟት ሰለማያውቅ ይህንኑ ገመና ለመሸፈን ስንል ብቻ ነው:: ስለዚህ ከ6 ወር በኋላ ለቅቆ ይወጣል» በማለት ለጊዜው ምንጮቹ ስሙን ያላወቁት ጠይም ሰውነቱ ደልደል ያለ የጄኔራል ማዕረግ ያደረገ ምላሽ እንደሰጣቸውና ሲለማመጣቸው እንደዋለም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ይኸው ስብሰባ በመኮንኖች ክበብ ተደርጐ በተጠናቀቀበት ምሽት ቁጥሩ ከ25 በላይ የሆነ የራሽያ ሰራሽ ኦራል መኪና ወታደሮች ተጭነው ወደ ሐረር መሰመር ሲጓጓዙ እንደነበር የአይን እማኞች ገልፀው የወያኔው ቡድን የጦሩ አባላት ላነሱት ጥያቄ ለማርገብ ብቻ ምላሽ የሰጠ ይሁን እንጂ አሁንም ወደ ሱማልያ ጦሩን እየላከ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው ወያኔ አሁንም ያለበትን ጦረኝነት ያሳያል ሲሉም ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ የመከላከያ ምንጮቻችን ገልፀዋል::

ከ25 ኦራል በላይ ወታደሮችን አሳፍሮ ወደ ሐረር መስመር የተጓጓዘ ከመሆኑም በላይ በተጨማሪ በርካታ የከባድ መሣሪያ በሎቤድ ቮልቮ መኪኖችም ተጭኖ ከኋላ ተከትሏቸው እንደሄደም የአይን እማኞች ገልፀዋል::

ባለፈው ሳምንት በመኮንኖች ክበብ ውስጥ በተደረገው በዚሁ ስብሰባ ላይ ሐሳብ ሲሰነዝሩ የነበሩት የጦሩ አባላት በሳምንት ውስጥ ከቤታቸውም ሆነ ከቢሯቸው ውስጥ ያልታዩ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮች ምናልባትም በደህንነቶች ታፍሰው ተወስደው ሳይታሰሩ እንዳልቀሩ ምንጮች ያላቸውን ስጋት ይገልፃሉ::

በተያያዘ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በማህበር ተደራጅተው ከ12 ዓመት በፊት ቦታ ተረክበው ቤት ሰርተው የነበሩትን ነዋሪዎች ሕጋዊ አይደለም በማለት የወያኔ ቡድን ለማፍረስ እየተሯሯጠ መሆኑ ታወቀ::

የፀረ ሙስና ኮሚሽን የተባለው መለስ ዜናዊ በ24 ሰዓት ውስጥ ያለምንም ዕቅድና ፕላን እንዲመሠረት ያደረገው መስሪያ ቤት ሰሞኑን 107 ማህበራት ሕገ ወጥ መሆናቸውን እያወጀ መሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን እያነጋገረ መሆኑ ታውቋል::

ለ12 ዓመታትና ከዚያም በላይ በይዞታነት ተሰጥቷቸው በማህበር ተደራጅተው እየተንቀሳቀሱ ያሉትና በየዓመቱም የሚፈለግባቸውን ግብር እየከፈሉ መሆኑ እየታወቀ ዛሬ የወያኔ ቡድን ገንዘብ ስለቸገረው ብቻ ሕጋዊ አይደሉም እያለ

ማወጁ ይህችን ሐገር በዘፈቀደ እየመሩ ያሉት አጋጣሚው የፈቀደላቸው የግለሰቦች ጥርቅም ነው ሲሉ አንድ አባት በንዴት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

መብራት፣ ውሃና ስልክ መስመሮች ተዘርግቶላቸው መደበኛውን ሁሉ አከናውነው ሕጋዊ ክፍያ እየከፈሉ ለ12 ዓመታት እና ከዚያም በላይ መኖር የጀመሩት እነዚህ ሰዎች ዛሬ ሕጋዊ አይደላችሁም ሊፈርስ ይችላል ተብሎ በመታወጁ ከፍተኛ ድንጋጤና ሐዘን ውስጥ ወድቀው እንደሚገኙ የታወቀ ሲሆን በዚህ 107 ማህበራት ስር ቢያንስ እያንዳንዱ ከ75 -100 የሚሆኑ ቤቶችን ያካተተ ሲሆን በአማካኝ ከ8ሺህ ቤቶች በላይ በስሩ ያሉ መሆኑን የገለፁት የዚሁ የማህበራቱ አባል በዚህ በ8ሺ ቤት ውስጥ በእያንዳንዱ ቤት በትንሹ 5 አምስት ሰው ቢኖር ከ40ሺህ በላይ ሰዎች እንዳሉት እየታወቀ 40 ሺህ ሰዎች ያለምንም መጠለያ አውላላ ሜዳ ላይ እንዲወድቁ ለማድረግ የወያኔ ቡድን መሯሯጡ በጣም የሚያሳዝን ነው ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::

በሌላ በኩል የወያኔው ቡድን ዲሞክራሲያዊ ምርጫ አድርጌያለሁ ለማለትና በአለም አቀፉ መንግስታትና በውጭ ማህበረሰብ ፊት የጠቆረ እና የጐደፈ ስሙን ለማደስ በማሰብ ብቻ በግዳጅ የምርጫ ካርድ ሕዝብ እንዲወስድ እያስገደደ መሆኑ ታወቀ::

ከሰኞ ጥር 12 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሽግግሩ የቀበሌ ተመራጭ ናቸው የተባሉ ባለሥልጣናት ቤት ለቤት እየተዟዟሩ የምርጫ ካርድ በግድ እየሰጡ ሲሆን ካርዱን አልወስድም ያለውን እያስፈራሩና ስም ዝርዝር እየለቀሙ መሆኑ ታውቋል::

በአራት ኪሎ በፒያሳና በስደት ኪሎ አካባቢ ተዘወውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን እንደገለፀው ከሆነ በየቤቱ ሰዎቹ በሌሉበት መዝገብ ወላጆቻችሁ ሲመጡ ስጧቸው በማለት እንደ ፀበል ቅሙሱ በግድ እያዳረሱ ሲሆን፣ ተገኝተው አንወስደም የሚሉ ወጣቶችን «በአደገኛ ቦዘኔ ፋይል አስከፍተን እናሳስርሃለን» እያሉ በማስፈራራት ላይ እንደሚገኙም ዘገባው አስረድቷል::

በተለያዩ ቦታዎችም እድሜያቸው ለምርጫ ያልደረሱ የ17 እና ከዚያም በታች የሆኑ ልጆች የምርጫ ካርድ እየተሰጣቸው መሆኑም ታውቋል::

በማያዝያ ሊደረግ በታሰበው የሚሚያ፣ የወረዳና የቀበሌ ምርጫ ሕዝቡ እንዲመዘገብ ጥሪ ቢተላለፍለትም አሻፈረኝ በማለቱ በኮንዶሚኒየም ቤቶች እና በፋብሪካዎች ደጃፍ ላይ ምዝገባ እንዲካሄድ ቢደረግም እንዳሰቡት ያልተሳካ በመሆኑ በቤት ቁጥር ቤት ለቤት እየዞሩ ምዝገባ ማድረጋቸው ታውቋል::

በቤት ቁጥር ቤት ለቤት እየዞሩ እንደ ቀበሌ ሬሽን በግዳጅ እያደሉ ሲሆን ወጣቶቹ አይመለከተንም ሲሉ « በአደገኛ ቦዘኔነት ክስ እንዲመሰረትብህና ሸዋ ሮቢት እንድትወረወር ትደረጋለህ» እያሉ እያስፈራሩ በግዳጅ እያደሉ ሲሆን፣

የመንግስት ት/ቤት መምህራኖችም ት/ቤቱን ለአንድ ቀን እየዘጉ የምርጫ ካርድ እንዲወስዱ ተገድደው እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

የውሸት ምርጫ አላደርግም ከዚህ በኋላ ምርጫ ምንም አይጠቅመኝም በማለት እያማረረ ያለው የአዲስ አበባን ሕዝብ በግዴታ ምርጫ ካርድ ካልወሰድክ ተብሎ ወያኔዎች ቁም ስቅሉን እያሳዩት ከመሆኑም ባሻገር ካርድ ካልወሰድክ እየተባለ የፈጠራ ክስ እየመሰረቱ ሊያስፈራሩትም በዝግጅት ላይ መሆናቸው ከየጣቢያው ሾልኮ የደረሰን ዘገባ አጋልጧል፡፡

እያስፈራሩም ቤት ለቤት እደላውን ቢያደርጉም ያሰቡት ሊሟላላቸው ያልቻለው የወያኔ ምርጫ ቦርዶች የምዝገባ መጠናቀቂያ ቀን ጥር 18 ቀን 2000 ዓ.ም የነበረ ቢሆንም በሕዝቡ እምቢተኝነት እንደታሰበው ባለመሆኑ የመመዝገቢያው ቀን ተራዝሞ እስከ ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ እንዲሆን ተወስኗል፡፡

ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ስብሰባ በአዲስ አበባ እንደሚካሄድና ለዚሁም ጥበቃ ይረዳ ዘንድ ሕዝቡ በውድም ሆነ በግድ ትብብር እንዲያደርግ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ተስፋዬ መረሣ ትዕዛዝ መተላለፉ ታወቀ፡፡

ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ለኢንተርኔት ባለቤቶች በየክፍለ ከተማው መሰብሰቢያ አዳራሽ በ9 ሰዓት እንዲገኙ ከፖሊስ የመጥሪያ ደብዳቤ የደረሳቸው እና በተባለው ቀንና ሰዓት ባለንብረቶቹ የተገኙ ሲሆን በዚህ ጊዜ በአሁን ሰዓት ፖሊስ ብቻውን መስራት እንደማይችልና ለዚህ ደግሞ የሕብረተሰቡ ትብብር እንደሚያስፈልግ ገልፀው በተለይ በኢንተርኔት የሚላላኩትን ሰዎች ለፖሊስ ጥቆማ እንድታደርጉ በማለት የደህንነት ስራ እንዲሰሩ መታዘዙ ታውቋል፡፡

«በአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ የሚካሄደውን የአፍሪካ መሪዎች ሥብሰባ ያለምንም ፀጥታ ችግር በሠላም እንዲከበር ከኢንተርኔት ካፌ ባለቤቶች እና ኃላፊዎች ጋር መወያየት አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ በማዘጋ ጣቢያው እንድትገኙልን የተለመደ ትብብራችሁን እንጠይቃለን» በሚል ጥር 14 ቀን 2000 ዓ.ም ደብዳቤው ለኢንተርኔት ባለንብረቶች የተበተነ ሲሆን፣ ይህ ደብዳቤ ተሰጥቶት የቀረ ሰው እንደ ከሀዲና ጠላት ተቆጥሮ አስፈላጊው እርምጃ እንደሚወሰድበት ፖሊሶች በቃል ጭምር ሲያስፈራሩ እንደነበረ የኢንተኔት ባለንብረቶች ገልፀው የተባለውም ስብሰባ የተካሄደ ሲሆን በዕለቱ ውይይት ሳይሆን ከፖሊስና ከደህንነት መስሪያ ቤት የመጣውን መመሪያና ትዕዛዝ በቀጥታ ከማስፈራሪያ ጭምር እንደተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡፡

በኢንተርኔት የሚጠቀሙትን ሰዎች ማንነት በአቅራቢያቸው ለሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ሪፖርት እንዲያደርጉ የስልክ ቁጥር ጭምር የተሰጣቸው ሲሆን፣ ይህንን በማይፈፅም ባለንብረት ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ እንደሚወሰድም አሳስበዋል፡፡

ጥርስ እንደሌለው አንበሳ የሚቆጠረው የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ እንደሚደረግ በተገለፁበት ሰሞን በርካታ ዜግነታቸው ለጊዜው ያልታወቁ አፍሪካውያን ወታደሮች ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንደገቡና ሌሊቱን ወደ አዋሽ አርባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ እንደተጓጓዙ ከቦሌ አየር ማረፊያ የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

አንዳንድ የቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ሰራተኞች እንግዶቹን ተቀብለው ለማነጋገር እንደሞከሩት ከሆነ ዜግነታቸውን ሊገልፁ አልፈጉም ነገር ግን ወደ ሞቃዲሾ ሊዘምቱ መሆኑን ነግረውናል ሲሉም ተደምጠዋል፡፡

ሞቃዲሾ በየቀኑ በከባድ መሣሪያና በአዳፍኔ እንደጌሾ እየተወቀጠች ያለች ሲሆን የሠላም አስከባሪ ኃይል የተባለው ጦርም ወደ ሞቃዲሾ በአየር እንዳይገባ የሞቃዲሾ የአየር ማፊረያ በሞርታር እየተደበደበ በመሆኑ አዲስ አበባ ላይ ሠፍሮ በኮንቮይ ውስጥ ውስጡን ወደ ሞቃዲሾ ለመግባት ሳይገደድ እንዳልቀረም እነዚሁ የቦሌ አየር ማረፊያ ሠራተኞች ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል፡፡

እንደመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ከሆነ ደግሞ ከቦሌ እየተወሰዱ አዋሽ አርባ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ እንዲሰፍሩ የሚደረጉት የሠላም አስከባሪ ኃይል የተባሉት ወታደሮች የኢትዮጵያን ድንበር በመኪና አቋርጠው ለመሄድ ከባድ ፈተና ስለሚሆንባቸው ወታደሮቹን የሚያጅብ ሌላ የወያኔ ጦር እስኪዘጋጅ ድረስ ለቀናቶች በዚያው በካምፑ ውስጥ ለመቀመጥ እንደተገደዱ ለማወቅ ተችሏል ብለዋል፡፡

አክለውም ከጥር 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተከታታይ ለ3 ቀናት ምሽት ቦሌ አውሮፕላን የሚደርሱት እነዚሁ ወታደሮች በሙሉ በአውቶቡስ ተጭነው ወደ አዋሽ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ የተወሰዱ ሲሆን፣ በምግብ አቅርቦትም ለጊዜው ተቸግረው እንደነበረና በተለይም በኦጋዴን በኩል ከፍተኛ ችግር መኖሩን የወያኔ ወታደሮች በነገሯቸው ጊዜ እጅግ ተደናግጠው በፍርሃት ተውጠው እንደነበረ ገልፀው አሁንም ከአዋሽ ጀምሮ እስከ ሞቃዲሾ ድረስ አጅቦ የሚያደርስ የወያኔ ጦር እስኪመጣ ድረስ በዚያው ለመቆየት መገደዳቸውንም ጭምር ገልፀዋል፡፡

ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ዛሬ ጥር 18 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ወታደሮቹ በዚያው በአዋሽ ካምፕ ውስጥ እንዳሉም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

***ማስታወሻ:-***

*1ኛ በአዲስ አበባ የኢንተርኔት ካፌ ባለንብረቶች የደህንነት ስራ እንዲሰሩ ታዘዙ*

*- ይህን ትዕዛዝ ያስተላለፈው የደህንነት ክፍል ኃላፊው አቶ ጌታቸው አሰፋና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ተስፋዬ መረሳ መሆናቸው*

*- ማንኛውም ኢንተርኔት ተጠቃሚ ግለሰብ በስውርም ሆነ በግልፅ እንዲታወቅ ግዴታ ተጣለ*

*- ሪፖርት ለማቅረብ በአካል ወይም በስልክ ቁጥር ተብሏል::*

*- የአፍሪካ የመሪዎች ስብሰባ ረቡዕ ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ይደረጋል::*

*2ኛ ከጥር 14 ቀን እስከ ጥር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ዜግነታቸው ያልታወቁ አፍሪካዊ ወታደሮች በሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን መድረሳቸው ታወቀ*

*- ሶስት ተከታታይ ቀናት የገቡት ወታደሮች ወደ አዋሽ አርባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ተጓጉዘዋል*

*- ወደሱማልያ ሊዘምቱ መሆኑ ተነገረ*

*- የሞቃዲሾ አውሮፕላን ማረፊያ በታጣቂዎች ከባድ መሣሪያ ቁጥጥር ስር መዋሉ በኮንቮይ መልክ ውስጥ ውስጡን በኢትዮጵያ ድንበር አቋርጠው ሊገቡ መሆኑ ተነገረ*

*3ኛ አንድ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የኢኮኖሚ ባለሙያ ለሥራ ጉዳይ ወደ ካናዳ ተጉዞ በዚያው ቀረ*

*- የፌዴሬሽን ምክር በኢኮኖሚ ዙሪያ ከፍተኛ ስራ ይሰራላቸው እንደነበር*

*- ተስፋዬ የተባለው ይኸው ግለሰብ የደኢህዴን (የደቡብ) ፓርቲ አባል እንደነበረ*

*4ኛ ነዳጅ በከፍተኛ ሁኔታ ጨመረ*

*- አንድ ሊትር ዋጋ 9 ብር ከ65 ሳንቲም ገባ*

*- ቀድሞ 7 ብር ከ77 ሳንቲም ነበር*

- **የ0.15 ሳንቲም የነበረው ዳቦ 0.35 ሳንቲም ገብቷል**
- **ሐገር ውስጥ የሚመረተው ጨው በኪሎ 50 ሳንቲም ጨመረ**
- **ትራንስፖርት በእጅጉ ሊያሻቅብ በመሆኑ ሕዝቡን ስጋት ላይ ጥሎታል፡፡**